

# ቤትና ቤተኝነት




መስከረም 2018
ቅፅ ፩ | ቁጥር ፫


ንስንስ ትኩረቷን በLBQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ በኩዊር ኢትዮጵያ የምትታተም መጽሔት

Nisnis - A quarterly magazine published by Queer Ethiopia focusing on LBQ issues

QUEER ETHIOPIA

ኩዊር ኢትዮጵያ

«ኩዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኩዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኩዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኩዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ' ኩዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።


queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

t.me/queeret


PRID

# ማውጫ




02



04 - 09



10 -12



13 - 15



16 - 19



20 - 23



24 - 27



28 - 29



30 - 33



34

# የአርታዒያን መልዕክት

የፕራይድ ባንዲራን ከኢትዮጵያ ሬስቶራንት ተሻግሮ ባለ መስኮት ላይ ሲውለበለብ ማየት፤ በባእድ ሀገር የተገኘ ብርሃን፤ ሊበሰር የሚገባ እይታ ነው። ይህን መመልከት ኢትዮጵያዊ ኩዊርን ከአመታት በኋላ እንድትተነፍስ ማድረግ መቻሉ በደስታ ያስነባል።

ያለመሳቀቅ የምንኖርበት ቤት ማግኘት እንደምንችል የሚያመላክት ተስፋ ነው።

እንኳን ወደ17ኛው የንስንስ እትም መጣችሁ። በዚህ እትማችን የቤትና ቤተኝነትን ትርጉም እንዳስሳለን። ለኩዊር ኢትየጵያውያን ቤት ቦታ ብቻ አይደለም። በየቀኑ ራሳችንን የምንጠይቀው ውስብስብ፤ ህመም ያለው እና ውብ ጥያቄ ነው። ቤት በጥላቻ ተሳደን ትተነው ልንሄድ የተገደድነው ቦታ፤ ለመኖር ስንል ለራሳችን የገነባነው መኖሪያ እና በአደገኛ ሀገር ውስጥ በየጥጉ የፈጠርነው ፍቅር ነው።

በዚህ እትም ያሉት ታሪኮች እንደሚያሳዩት ደህንነታችን ሊጠበቅባቸው የሚገቡ ቦታዎች ብዙ ጊዜ የጥላቻ እና ጥቃት መገኛ ይሆናሉ። የቤተሰቦቻችን ቤት "ትልቅ ሚስጥር" የምንደብቅበት ቦታ ሊሆን ይችላል። የልጅነት ቤተክርስቲያናችን ቤታችን ከመሆን የመሸማቀቃችን ምንጭ ይሆናል። የዩኒቨርስቲ ካምፓሶቻችን፤ መማሪያችን ሊሆኑ ሲገቡ ሳቃችንን፤ ስታይላችንን እና ንግግሮችቻችንን የምንደብቅባቸው "የህመማችን ሰበብ" ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ጸሀፊያችን እንደገለጸችው "ኢትዮጵያ ለኩዊሮች ቤት አይደለችም"። ሰውነታችንን የመጀመሪያ እና አንዳንዴም ብቸኛ ቤታችን አድርገን ለመኖር እንገደዳለን።

ይሁንና በዚህ ሁሉ መገፋት እና መከዳት ውስጥ የራሳችንን ቤት በጽናት እንገነባለን። ይህ እትምም በብዙ መንገዶች ስለምንገነባቸው ቤቶች ምስክር ነው። ለአንዳንዶች ቤት ሰው ነው፤ ትለናለች አንድ አምደኛችን። "ሰው የማይደርስበትን ቦታ ፈጥረናል። ፍቅር እዚህ ደህንነቱ የተጠበቀ በመሆኑ ይህ ቤታችን ነው" ስትል ስሜቱን ገልጻለች።

ለሌላዋ ባለታሪካችን ቤት ማለት ጩኸት እና ግርግር የበዛበትን ኮንሰርት የምትወዱት ሰው በሚስጥር እጃቸውን ስለያዛችሁ "ሰላማዊ ብቸኝነት" የሚሰማበት ቦታ የሚያደርግ ስሙት ነው። የፍቅረኛዋን እጅ መንካቷ ብቻ ሁኔታን የሚቀይር ሀይል ነበረው።

ልክ እንደዮሀና ቤትን በራሳችን ውስጥም ልናገኝ እንችላለን። ዮሀና ከራሷ ጋር ጊዜ በማሳለፍ እውነተኛ የቤተኝነት ስሜት የማንንም ፍቃድ እንደማይጠይቅ ታሳየናለች። ቤትን በማህበራዊ ሚዲያ፤ ድንበር አቋርጠው በሚገኙ መርጠን ቤተሰብ ባረግናቸው ሰዎች ውስጥ እናገኘዋለን። መልሰን ባገኘነው እምነታችን፤ በሌዝቢያን ፓስተር በሚመራ ቸርች ውስጥ ባገኘነው አገልግሎት፤ የቀስተደመና ምልክት ባደረገው ፒያኒስት ሙዚቃ ውስጥ ሁሉ ቤተኝነት አለ።

ለሌሎች ቤት በስደት የሚገነባ ነው። ኬንያ ውስጥ በነጻነት ከፍቅረኛዋ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዛ መሄድ በመቻሏ እና የማታውቃቸው ሰዎች "የፈለገችውን የመሆን መብት አላት" ብለው ሲከራከሩላት የተሰማት ስሜት ቤቴ ነው ትለናለች ሌላ ባለታሪካችን። ቤት እንደኢትዮጵያ ጨለማ ያደበዘዘው ሳይሆን በብርሀን የተሞላ ህይወትን ማሰብ የመቻል ነፃነት ነው። በማይታወቅ ወደፊት ውስጥ አደጋን መጋፈጥም ነው።

ይህን የንስንስ እትም ጽናታችሁን ያሳያል እና በኩራት እንደሚሞላችሁ ተስፋችን ነው። በአደጋ ውስጥም ፍቅርና ደህንነትን ማግኘት እና መገንባት የምንችልበትን አቅም የሚያወድስ እትም ነው። በተለዋዋጭ ሁኔታ ውስጥ ቤታችንን መገንባት በመቀጠል የራሳችን ቤት ገንቢ እኛው መሆናችንን እናረጋግጣለን። በተስፋ እና ቁርጠኝነት ከፍ በማለት ተስፋ እንደማንቆርጥ እናሳያለን።

በድጋሚ ንስንስን ስለምታነቡልን እናመሰግናለን። ታሪካቸውን ላጋሩን ሁሉ ምስጋናችን ከልብ ነው። ያለእናንተ ይህ እውን አይሆንም ነበር።

መልካም ንባብ!

# የቤትን ትርጉም ፍለጋ





“ብቻዬን
ስሆን
የራሴ ቤት
እንደሆንኩ
ይሰማኛል”

– ዮሃና

ቤት መሰረታዊ ፍላጎት ነው፤ ደህንነታችን የሚጠበቅበት እና ቤተኝነት እንዲሰማን የሚያደርግ ቦታ። ለብዙ ኩዊር ኢትዮጵያውያን ግን ይህ ቀላል ነገር አይደለም። ደህንነትን ሊሰጡን የሚገቡ ሰዎች እና ቦታዎች እኛነታችን መቀበል ሲያቅታቸው ከባድ ምርጫን ለመምረጥ እንገደዳለን፤ ይህም መደበቅ፤ መሸሽ ወይም የቤትን ትርጉም መቀየር ሊሆን ይችላል።

ይህ ታሪክ ከነዚህ ምርጫዎች በመነሳት ስለተጀመሩ መንገዶች ነው። ዮሀና የቤትን ስሜት በራሷ ውስጥ መገንባት ችላለች። እውነተኛ እሷነቷን የምትሆንበት የራሷን ቦታ ፈጥራለች። ጃምዚ ደግሞ በብዙ መስዋእትነት እና ህመም ለደህንነቷ ስትል ኢትዮጵያን ትታ ለመሄድ ተገዳለች።

እነዚህ ሁለት ታሪኮች ስለጽናት ናቸው። እዚህ ልትሆኑ አይገባም ብሎ የሚያርቅ ሀገር ውስጥ የኔ የሚሉትን ቦታ መፍጠር ጽናትን ይጠይቃል። በዚህ ውስጣዊ እና ውጫዊ ጫና ውስጥ ተስፋ ትልቅ ቦታ አለው፤ የተሻለ እና ራሳችንን ከመሆን እና ደህንነታችን ከማስጠበቅ አንዱን ለመምረጥ የማንገደድበት ነገ ይመጣል።

በዮሃና እና ጃምዚ የህይወት ጉዞ፤ የቤተኝነት ስሜት የሚሰጥ ሳይሆን የሚገነባ እንደሆነ እንረዳለን። ይህ የመገንባት ሂደትም የሚቀበለን አለም እንዲኖር እንዳለ ተስፋ የመጣ ነው።

ዮሃና፡ በእኔነት ውስጥ ያለ ቤት

ለዮሃና ቤት የሚለው ቃል ባለፉት አመታት ትርጉሙን ቀይሯል። ከዚህ በፊት ቀለል ባለ አገላለጽ ቤተሰቦቿ የሚኖሩበት መኖሪያ ቤት አድርጋ ትረዳው ነበር። ራሷን ይበልጥ እየተረዳች በመጣች ቁጥር ግን ይህ ቀላል ትርጉም ነጻነት የማይሰጥ እና የማይመች መስሎ ተሰማት። ፍቅር የነበረ ቢሆንም በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ እና እንድትኖር ከሚጠበቅባት ህይወት ጋር የተያያዘ ነበር።

ዛሬ ላይ ቤት ለራሷ የምትገነባው ነገር ሆኗል። ግኡዝ አካል ሳይሆን በውስጧ ያለ ስሜት እንደሆነ ተረድታለች። ዘና የማለት እና ራሷን በነጻነት የመሆን ስሜት ነው።

ስሜቱን ስትገልጽ የሚሰማት እረፍት ከድምጽዋ መረዳት ይቻላል። “ብቻዬን ስሆን ማንም ሰው አይፈርድብኝም” ዝም ባለው ክፍሏ ውስጥ የውጪው አለም ጸጥ ይላል። እዚህ መጸለይ፤ ሜዲቴት ማድረግ ወይም ራሷን መግለጽ ሳይኖርባት የምትፈልገውን ፊልም መመልከት ትችላለች። ይህ የብቻ ነጻነት የሚጠበቅባትን ሆና እንድትገኝ ከሚያስገድዷት ሁኔታዎች የምታገኘው እረፍት ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ቤተኝነት ሊሰማኝ ይችላል ብላ ባሰበችባቸው ሌሎች ኩዊር ሰዎች ባሉባቸው ቦታዎችም የሚፈጠሩ ናቸው።

የብቻዋን መደበቂያ የፈለገችበት አንዱ ምክንያት ህይወቷ በየእለቱ ትኩረት የሚበዛበት መሆኑ ነው። ከፍቅረኛዋ ጋር የምታደርገው የስልክ ንግግር ሳይቀር ሰው እንዳይሰማ ከሚደረግ ጥንቃቄ የጸዳ አይደለም። የሰዎችን ፊት በደንብ ተመልክታ ለመረዳት ትሞክራለች። “ደህንነት እንዲሰማኝ መጀመሪያ ሰላም እስኪሉኝ ጠብቄ ሁኔታቸውን ከገመገምኩ በኋላ ነው” ስትል ትናገራለች። የቤተሰብ መሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ለሷ ከማሰብ ከሚመጡ እና የወደፊት ህይወቷን የተመለከቱ ጥያቄዎች የተሞሉ ናቸው። መች እንደምታገባ፤ እንደምትወልድ ትጠየቃለች። ጥያቄዎቹን ለመመለስ ታሪክ ለመፍጠር ትገደዳለችለለ

“እነዛ ከባድ ጊዜያት ለቤቴ የከፈልኳቸው መስዋእትነቶች ናቸው።”

ጃምዚ

“የወንድ ፍቅረኛ አለኝ ብዬ ታሪክ እፈጥራለሁ” ስትል ዮሀና ራሷን ለመጠበቅ ስትል ምን ያህል ርቀት እንደምትሄድ ትናገራለች።

የውስጧን አለም ደህንነት ለማስጠበቅ የእለት ተእለት ልምዶች አዳብራለች። ሜዲቴት ማድረግ እና መጸለይ ከመንፈሳዊነታቸው ባሻገር ከራሷ ጋር ያላትን ግንኙነት የምታጠነክርበተ እና መሰረቷን የምትገነባበት ነው። ውስጣዊ ሰላሟ ከደፈረሰ የውጪው አለም ይበልጥ አስፈሪ እና ከባድ እንደሚሆን ታውቃለች።

ይህ ጉዞ ወደአንድ ጠንካራ መረዳት መርቷታል። ለረዥም ጊዜ በተለያዩ አለማት ቤተኛ ለመሆን ከሞከረች በኋላ የሚያዛልቃት እና የእኔ የምትለው በውስጧ ያለው ቤት እንደሆነ ተረድታለች።

”ብቻዬን ስሆን የራሴ ቤት እንደሆንኩ ይሰማኛል” በማለት ዮሀና ስሜቷን ትገልጻለች።

ማንም ሊያባራትም ሆነ እንድትኖር ከራሷ ውጪ ፍቃድ የማትጠይቅበት የራሷን ቤት ልትገነባ ችላለች።

ጃምዚ፡ የተስፋ እና የቤተኝነት ጉዞ

ለረዥም ጊዜ ቤት ለጃምዚ... ቤት፤ ግኡዝ አካል ነበር። ከሰፈር ልጆች ጋር ኳስ የተጫወተችበት አቧራማ ሜዳ፤ የእናቷ ሽሮ፤ በሚያውቋት እና የምታውቃቸው ሰዎች የመከበብ ስሜት ቤት ሲባል ወደአምሮዋ የሚመጡ ምሳሌዎች ነበሩ።

ይሁንና ይህ “ቤት” ያስጨንቃት ጀመር። አከራይዋ እሷን እና ጓደኛዋን እያየ የጠየቃትን ስሜት እና በውስጧ የተፈጠረውን የመረበሽ ስሜት አትረሳውም።

“መጥታ “ጌይ ናችሁ;” ብላ ጠየቀችን” ስትል ታስታውሳለች። “እንዳልገባው ሆንኩ፤ ስለምን እንደምታወራ እንዳላወቀ ሆኜ





አሳለፍኩት።”

በዛ ቅጽበት ቤቴ ብላ የምታስበው የምትከፍልበት ቦታ ደህንነቷ የሚጠበቅበት እንዳልሆነ ተረዳች። ለመኖር መዋሸት የምትገደድበት ቦታ ነበር።

ከምትኖርበት የክልል ከተማ ወደ አዲስአበባ ስትመጣ ይህን ያህል አደጋ እጋፈጣለሁ ብላ አስባ አታውቅም ነበር። ከተማው ውስጥ ያለው የጥላቻ ዘመቻ እየበረታ ሲመጣ መንገድ ላይ ብቻዋን መንቀሳቀስ በራሱ ያስፈራት ጀመር። “ለምን እንደወንድ ትለብሻለሽ” የሚሉ ድንገተኛ ጥያቄዎች ፍርሀቷን የሚያባብሱ ነበሩ።

ኢትዮጵያን ትታ የሄደችው ዝም ባለ እና በእንባ በተሞላ መንገድ ነበር። ወደኬንያ ስትጓዝ በውስጧ አንድ ተስፋ ነበር፤ ራሷን የምትሆንበት ቦታ ማግኘት። እውነታው ግን አስደንጋጭ ነበር።

“ኬንያ ምቹ የሚባል ቦታ አይደለም” ስትል በድካም ትናገራለች።

በናይሮቢ ጎዳናዎች ላይ መጠቃትን ከመፍራቷ የተነሳ አይኖቿን መጨፈን እስኪያቅታት ድረስ ካስጨነቃት የደህንነት እጦት ጨምሮ ብዙ ውጣውረዶች አሳልፋለች። ለመኖ ስትል መኪና ከማጠብ ቆሻሻ እስከመሰብሰብ ድረስ ብዙ ስራዎች ሰርታለች።

“ለመኖር ስል ብዙ ከባድ ነገሮች አድርጌያለሁ” በማለት ሁኔታውን ታስረዳለች።

በእዚህ ችግር ውስጥ ግን በውስጥዋ ጠንካራ የቤት መሰረት እየተገነባ ነበር። ቤት ማለት ስለአንድ ሀገር ወይም መኖሪያ ቤት ሳይሆን በራሷ መንገድ አንድ ተጨማሪ ቀንን መኖር መቻል እንደሆነ አወቀች።

“እነዛ ከባድ ጊዜያት ለቤቴ የከፈልኳቸው መስዋእትነቶች ናቸው” ትላለች። ጥንካሬዋ በድምጽዋ ውስጥ ይሰማል። ኩዊር ሰዎች እንደሷ ዋጋ እንዲከፍሉ የማታስገድድ ኢትዮጵያ ወደፊት እንደምትኖር ተስፋ ታደርጋለች።

ለአሁን ግን ቤት ማለት በጽናት እና በጀግንነት የተሞላው በውስጧ ያለው በሄደችበት ሁሉ የማይጠፋው እሳት ነው።

# ቤት፡ እፎይ የምንልበት ቦታ

ቤት የሚለው ቃል ያስገርማል በተለይም ደህንነት ሊሰማን የሚገባበት ቦታ መሆኑን ስናስብ ከእውነታው ጋር ያለው ርቀት የሚደንቅ ነው። ኢትዮጵያ ለኩዊሮች ቤት አይደለችም። ከምንወዳቸው ሰዎች፤ የአምልኮ ቦታዎች እና ከመንግስት ብዙ ጥቃት አስተናግደናል። በ2011 እኛን ተቃውሞ ከተደረገው ጋዜጣዊ መግለጫ ጀምሮ እስከ2019ኙ ቶቶ ቱርስ ብሎም የ2023 ግበረሰዶምን እቃወማለው ዘመቻ የማያቋርጥ የጥላቻ ማእበልን ተጋፍጠናል። የተጠቀሱት አጋጣሚዎች ተመሳሳይ መልእክት የያዙ ናቸው። “ይህ ቤታችሁ አይደለም፤ እዚህ መሆን አይገባችሁም”

እነዚህ የተቀነባበሩ የማስፈራራት ዘመቻዎች የተለያዩ ቢሆንም አንድ የሚያደርጋቸው ሰፊ አላማ ግን እኛን ከሀገሪቱ ማጥፋት ነው። በፕሮፓጋንዳ እና ህዝባዊ ውግዘት መኖራችንን መልሶ ለማጥቃት ብቻ በማንሳት በገዛ ሀገራችን ባእድነት እንዲሰማን አድርገውናል። “ቤት” የሚለውን ቃል እንደመሳሪያ ተጠቅመውበታል። መጠጊያ እና መሸሸጊያ ሊሆነን የሚገባውን ቦታ የምንሸሸው እንዲሆን አድርገዋል።

ደህንነት ሲጠፋ ለመኖር ስንል መደበቅ እንጀምራለን። ንግግራችን የተመጠነ፤ ሳቃችን ጥንቃቄ የተሞላበት ይሆናል። ከማህበረሰቡ ራሳችንን ማግለል እና በነጻነት አብሮ ይኖር የነበረው እኛነታችንን መደበቅ ይከተላል። የቤተሰብ ዝግጅቶችን መቅረት፤ ጥያቄ አለመመለስ፤ ከማህበራዊ ሚዲያ ላይ የፍቅር መገለጫዎች ማጥፋትም ሌላው ጥንቃቄ ነው። ይህ መደበቅ እየከበደ ይመጣል፤ በመንገዳችን የሚከተለን ሰው እንዳለ ዞር እያሉ በማየት፤ ካፌ እና ምግብ ቤቶች ውስጥ ፊት ማየት፤ የአጋራችንን እጅ በሰው መሀል ከመያዝ በፊት አካባቢውን መቃኘት የተለመደ ይሆናል። ፍቅር እና መቀራረብ በጥንቃቄ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ይሆናሉ። ከፍቅር አጋር ደግሞ ይህን ጥንቃቄ ይበልጥ ያጠነክረዋል። የእለትእለት ኑሯችን በስሌት እና ተደብቆ መኖር እንደተፈጥሮ በመለማመድ ይሞላል።

ቤትን መሸሽ እና እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በስሌት ማድረግ ያማል።



አጋሮቻችን “እንዴት ነው የምትኖሩት; የቤተኝነትን ስሜትን እንዴት ታገኙታላችሁ ሲሉ ይጠይቃሉ” ጥያቄያቸው ውስጥ አለማመን አለ።

“እንዴት እንደምትወጡት አላውቅም” አይነት አለማመን!

ብዙ ሚስጥር፤ ያልተነገሩ ታሪኮችን እና ፍርሀትን ይዘው ስለሚኖሩ ኩዊር ነፍሶች አስባለሁ። ከውጪ ያለው አለም አደገኛ ሲሆን ሰውነታችን ብቸኛ መደበቂያችን ይሆናል። ትውስታን እና ፍላጎታችንን የምናስቀምጥበት ቦታ ነው። ተደብቄ ያለፍኳቸውን ግልምጫዎች እና ያልተናገርኳቸውን የፍቅር ታሪኮች የሚያስታውሰው ሰውነቴ ነው። ትኩረት ሳንስብ እንዴት መራመድ እንዳለብን ከፍቅር መደበቅን፤ በአደባባይ በዝምታ ማዘንን የሚያስታውሰን ሰውነታችን አይደል፤ በዚህ ሁሉ ስሌት ውስጥ ግን ጸጋም አለ። መኖር እና ማፍቀርን የመምረጥ ጸጋ። በፍርሀት እና ነጻነት መሀል ያለው ውዝግብ በራሱ እምቢተኝነት ነው።

ድንበር አቋርጠን እንድገናኝ ስለሚያደርገን ሶሻል ሚዲያ አስባለሁ። ትንሽዋ መደበቂያችን። ከረዥም የማስመሰል ቀን በኋላ ስልካችንን ከፍተን እፎይ ወደምንልበት አለም እንገባለን። ከሙሉ ቀን በኋላ የጡት ማስያዣን የማውለቅ ወይም ከረዥም የመንገድ ጉዞ በኋላ ቡትስ ጫማን የማውለቅ አይነት ሰላም አለው። እዚህ ካፌ ውስጥ እንደምንደበቀው ሳይሆን በሙሉ ድምጻችን እውነታችንን እንናገራለን። እኛ ብቻ የሚገባንን ሜም እንጋራለነ። የፍቅር ታሪካችንን ያለፍርሀት እናወራለን። በነዚህ ግንኙነቶች ውስጥ ከመረጥናቸው ሰዎች ጋር ቤተሰብ እንመሰርታለን። ሰፊ፤ ውብ እና ብዙ አይነት እህት እና ወንድሞች ያሉበት ቤተሰብ ይኖረናል። የጥላቻ ዘመቻ ሲነሳ መልእክት የሚልኩ፤ እንድንበላ፤ እንድናርፍ፤ እንድንተነፍስ የሚያስታውሱን ቤተሰቦች እናገኛለን። ታሪካችንን ሳይገምቱን ያደምጡናል። ሰውነታችን አዲስ ቤትን ይለምዳል። በአካል አግኝተን የማናውቃቸውን ጥንዶች አመታዊ የፍቅር በአል እናከብራለን፤ እንኳን አደረሳችሁ እንባባላለን፤ ፊታችን የማይታይበትን ወይም የሚለየን ምልክት የሌለበትን ፎቶ እንላላካለን። በዚህ የግንኙነት መረብ ውስጥ አዲስ ቤት እናገኛለን። ሁሉ የተሟላለት አይደለም ግን እውነተኛ እና ህያው ነው።

እነዚህ ዲጂታል መረቦች በርቀት ያለ ፍቅርንም ይይዛሉ። አብዛኞቻችን የፍቅር አጋሮቻችንን ያገኘነው በዚህ የኦንላይን መድረኮች ነው። አንድ ኩዊር ሴት “በዚህ ሁሉ ጥላቻ ውስጥም ፍቅሬን ማግኘቴ እንዲቀለኝ አድርጓል” ስትል ነግራኝ ነበር። የኩዊር ፍቅር በኢትዮጵያ ያለውን ከባድ ህይወት በተወሰነ መልኩ ያቀለዋል።

**ከምንወዳቸው ሰዎች፤ የአምልኮ ቦታዎች እና ከመንግስት ብዙ ጥቃት አስተናግደናል።**

የፍቅር አጋሮች መደበቂያችን ይሆናሉ። ለአንዳንዶች አብረው የሚኖሩበት አፓርትመንት ወይም የኪራይ ክፍል በመተሳሰብ የተሞላ ቤታቸው ይሆናል። ጥላቻ የሌለበት እና ማን እንደሚመጣበት የምንፈቅድበት፤ ያለፍርሀት የምንደሰትበት ቦታ ነው። ከመረጥናቸው ቤተሰቦች ጋር የሳምንቱን መጨረሻ እና በአላትን የምናሳልፍበት የሞቀ የደመቀ ቤት ይሆናል።

መኖር እንደማይገባን ቦታ አብሮ መኖር የተቃውሟችን አንዱ መገለጫ ነው። የፍቅር አጋራችንን ወገብ ይዘን፤ እየተሳሳምን በምንወደው ሙዚቃ እንደንሳለን። ሳንደባበቅ በነጻነት የኩዊር ፊልም እናያለን። የተለመደ የሚመስልን ህይወት በነዛ ግድግዳዎች ውስጥ ብቻ በነጻነት ስለምንኖረው ልዩ ያደርገዋል፡

በስደት ስላለ ህይወት አስባለሁ። ብዙ ጓደኞቻችን አካላዊ እና ስሜታዊ ጥቃትን ሽሽት የሚያውቁትን ሁሉ ትተው ለመሰደድ ተገደዋል። የዚህ አይነት ሽሽት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በአንድ በኩል ያለፍርሀት መኖር እንደምንችል በማሰብ ቀለል እንዲለን እና ነጻነት እንዲሰማን ይሆናል፤ በሌላ በኩል ያጣነውን በማሰብ ሀዘን ይሰማናል።

ቤትን ከመሰረቱ ጀምረን መገንባት ይኖብርናል። አዳዲስ መንገዶች እና የአነጋገር ዘይቤን እንማራለን። ስማችንን እንዳዲስ ማለትን እንለምዳለን። በምርጫ ያገኘናቸውን ቤተሰቦቻችንን እና አብረን የምንስቅ እና የምንጫወት የእኛ የምንላቸውን ሰዎች እንናፍቃለን። እንደዛም ሆኖ በስደት ውስጥንም ደስታን የምናገኝበትን መንገድ እንፈልጋለን። ከሌሎች ኩዊር ኢትዮጵያውያን ጋር በትንንሽ ድብቅ ድግሶቻችን ሙዚቃችንን ከፍተን በእስክስታ እና ጉራግኛ እንጨፍራለን። አብረን እንጀራ እንበላለን ቡና እንጠጣለን፤ ቀጣይ ስለምንገናኝበት ዝግጅት እቅድ እናወጣለን።

እንደማንኛውም ዜጋ ተቀባይነትን ማግኘት እና ራሳችንን ማስረዳት ሳይኖርብን ወይም ማንነታችንን ሳንደብቅ መኖን የመሰለ ነገር የለም። ቢሆንም ግን ቤተኝነት እንዲሰማን የምንጠቀማቸው የተለያዩ መንገዶች ውስጥ ትልቅ ሀይል አለ፤ ይህ እኛነታችን ነው።

ቤት የተወለድንበት ሳይሆን እፎይ የምንልበት ቦታ ነው።

# የኩዊር ፍቅር በኢትዮጵያ ያለውን ከባድ ህይወት በተወሰነ መልኩ ያቀለዋል።


ካምፓስ፡ የሰቀቀን ቦታ

ኢትዮጵያ ውስጥ ኩዊር ተማሪ መሆን በህይወቴ ከባድ ከምላቸው ነገሮች አንዱ ነው። ማህበረሰባችን ለኩዊር ባለው ጥላቻ የሚታወቅ ነው። ካምፓስ ውስጥም የተለየ ነገር የለም። በነጻነት ኩዊር ስለመሆን ማውራት አይታሰብም። ስለሁኔታው ጥሩ ነገር መናገር ራሱ አደጋ ውስጥ ሊከት ይችላል።

በነጻነት ማፍቀር እና የፍቅር ግንኙነት መጀመር ደግሞ በጭራሽ የማይሆን ነው። አብዛኞቹ ተማሪዎች በሀይማኖት እና ባህል የተቀረጸ ማህበረሰብ ውስጥ እንደማደጋቸው አእምሯቸው ለብዙ ነገር ክፍት አይደለም።

በካምፓስ ሙሉ ደህንነት ተሰምቶኝ አያቅም። ደህንነታችን የተረጋገጠ አይደለም። ራሳችን መደበቅ ያለብን ለእዛ ነው። በእርግጥ የቃላት ጥቃት ያሳምማል፤ ትልቁ ፍርሀት ግን ሰዎች ኩዊር መሆኔን ቢያውቁ ምን ሊያደርጉኝ እንደሚችሉ ማሰብ ነው። አካላዊ ጥቃት ሊደርስብኝ የሚችልበት እድል ከፍተኛ ነው። የሰዎችን ህይወት ሊያሳጣ የሚችልበት ሁኔታ አለ። ይህ ፍርሀት እንዴት እንደምንቀሳቀስ፤ እንደምሆን እና እንደምናገር እንድጠነቀቅ ያደርገኛል።

በካምፓስ ሰራተኞች እና ፋኩልቲውን ጨምሮ ማንም ሰው በማንኛውም ሁኔታ ለእኛ ቦታ እንደማይሰጥ ግልጽ ነው። እኔም አልጠብቅም። ግን እድለኛ የሆንኩበት አንድ ነገር አለ፤ ይኸውም ስለእኔ የሚያውቁ የቅርብ ጓደኞች አሉኝ። ሁሉንም ነገር እንድችል ያግዙኛል። ከእነሱ ጋር መተንፈስ እና መሳቅ እችላለሁ። አብረን ፊልም እናያለን፤ እንጫወታለን እንዲሁም ስለብዙ ነገር ስናወራ ምሽቶችን እናሳልፋለን። በዚህ ጠባብ ጓደኝነት ውስጥ ደህንነት ይሰማኛል፤ እንደተረዱኝ አስባለሁ። ይህም የካምፓስ ህይወትን አስደሳች እንዲሆን አድርጎልኛል።

ሆኖም ራሴን መደበቅ አድካሚ ነው። “ጌይ ኢነርጂ” ላለመስጠት እሞክራለሁ፤ አንዳንዴ ግን ማስመሰል ከባድ ነው። ለመኖር ስል ያልሆንኩትን ሰው እንደሆንኩ መሆን ወይም እኔን በማይገልጹኝ ነገሮች ራሴን መደበቅ አልፈልግም።

ለምሳሌ ተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ከሆኑት ጓደኞቼ ጋር ስለፍቅር ግንኙነት ማውራት ለእኔ በጣም ከባድ ነው። ስለጉዳዩ ውይይት ከተነሳ ባልስማማበትም ራሴን በአዎንታ መነቅነቅ እና ሃሳባቸውን የሚደግፍ አስተያየት መስጠት አለብኝ። በእርግጥ ወንዶችም ይማርኩኛል፤ ግን አካታች ያልሆኑትን ርእሶች ማለቴ ነው፤ ስለተቃራኒ ጾታ ፍቅር ብቻ የሚደረጉ ንግግሮች እና እንደእኔ ላሉ ሰዎች ያለውን ጥላቻ መስማት ከባድ ነው።

ካምፓስ በነበርኩባቸው አመታት ከሰው ጋር ሁኚ እንዳይሉኝ ስል የወንድ ጓደኛ እንዳለኝ አስመስል ነበር። ጥያቄያቸው በጣም አሰልቺ ነበር፤ በትንሹም ቢሆን ኩዊር መሆኔንም ሆነ እንደምደግፍ እንኳን የሚያመላክት ነገር እንዳይገብኝ መጠንቀቅ ነበረብኝ። በአለባበሴ ጭምር ማህበረሰቡ ለሴቶች ልክ ነው ብሎ ካስቀመጠው መስፈርት ላለመውጣት እሞክር ነበር። አነጋገሬ፤ ጸባዬ፤ አካኋኔ ሁሉ ለመኖር ስል እኔን ያልሆንኩባቸው መንገዶች ነበሩ።

ያለፍርሀት ራሴን መሆን የምናፍቅባቸው ጊዜዎች ነበሩ። በነጻነት እውነተኛ ማንነቴን ሆኜ መኖር ያሰኘኛል። ናፍቆት እና ብስጭት አለበት፤ ያለማመንታት ራሴን የመሆን ናፍቆት እና እንድደበቅ የሚያደርጉኝ ነገሮች የሚፈጥሩብኝ ንዴት። ራሴን “ስተም ገርል” ብዬ ነው የማስበው እና አንዳንዴ ጸጉሬን ስለመቆረጥ እና የምፈልገውን ቀለም ስለመቀባት አስባለሁ፤ አፍንጫዬን ብበሳ እመኛለሁ፤ ሰፋፊ ልብሶችን በፕራይድ ቀበቶ ስለማድረግ አልማለሁ። ትንንሽ ግን በማንነቴ ምቾት እንዲሰማኝ የሚያደርጉ ነገሮችን እናፍቅ ነበር። ሰዎች ያለምንም ጥላቻ እና ማግለል ትክክለኛ እኔን እንዲያዩኝ መፈለጌ ነበር። ኩዊር መሆኔ የእኔ ነው። መሆኔን ለማረጋገጥ የሌሎች ማረጋገጫ አያስፈልገኝም። ግን እንደማንኛውም ሰው በአለም ላይ ራሴን ሆኜ፤ ሌሎች ብዙም ቦታ የማይሰጡትን በሰዎች ተቀባይነት የማግኘት ስሜት አግኝቼ መኖር ይገባኛል።

እንደኔ ላሉ ኩዊር ተማሪዎች ሁኔታዎችን የተሻለ የሚያደርግላቸው ነገር ቢሆን መከበር እና መረዳት ናቸው። ለቅርብ ጓደኛዬ እና የክፍል ተጋሪዬ ስለኩዊርነቴ

ስለነገርኳት ጊዜ አስታውሳለሁ። የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ነበረች ግን አብራኝ የኩዊር ፊልሞችን ትመለከት እና በአጠቃላይ ስለኩዊርነት ታዋራኝ ነበር። ከሌሎች በተቃራኒ በውስጧ ጥላቻ እና መፍረድ አልነበረም፤ አጋር ብዬ ስጠራት በኩራት ነው። ለረዥም ጊዜ እሷንም ዋሽቻት ነበር፤ በተለይም ደግሞ አብራን አንድ ዶርም የምትኖር ሌላ ሴት ዴት እያደረኩ ስለነበር አልነገርኳትም። ከጊዜ በኋላ ግን እየዋሸኋት መቀጠል አልቻልኩም። ማታ ማታ የእግር ጉዞ የማድረግ ልምድ ነበረን። አንድ ቀን እየተራመድን ኩዊር እንደሆንኩ ነገርኳት። ድምጼ እየተንቀጠቀጠ ነበር፤ በጣም ፈርቼ ነበር ግን ደግሞ ነጻነትም ነበረው።

አላንገራገረችም፤ አቀፈችኝ፤ እንደምትወደኝ ነገረችኝ። በዛ ቅጽበት ማስመሰል እንደሌለብኝ በማሰብ ነጻነትነ ተሰማኝ፤ ራሴን ሆኜ ነበር።

ሁሉንም ሰው እንደዚህ አይነት ጓደኛ እንዲሆኑ መጠየቅ ከባድ ሊሆን ይችላል። ቢያንስ ግን ካምፓስ ውስጥ ያሉ ሰዎች ባይስማሙ ራሱ በሰላም እንድንኖር እንዲተዉን እፈልጋለሁ። ምክንያቱም ፍቅር ፍቅር ነው። ተመሳሳይ ጾታን ማፍቀር ምንም ችግር ሊኖረው አይገባም።

ያለፍርሀት ራሴን መሆን የምናፍቅባቸው ጊዜዎች ነበሩ። በነጻነት እውነተኛ ማንነቴን ሆኜ መኖር ያሰኘኛል። ናፍቆት እና ብስጭት አለበት፤ ያለማመንታት ራሴን የመሆን ናፍቆት እና እንድደበቅ የሚያደርጉኝ ነገሮች የሚፈጥሩብኝ ንዴት።



# ቤቴ እሷ ናት

የእረፍት ቀናችንን
ያለንን ምግብ በማብሰል
እናሳልፋለን። ምስር፤
ጎመን እና ጥብስ።
ቡናችንን እንጠጣለን።
ስለሁሉም እና ስለምንም
እናወራለን። ከላይ
ሲታይ ቀላል ነገር
ይመስላል ለእኛ ግን
ከምንም በላይ ነው።
አለም የማትደርስብንን
ቦታ ፈጥረናል።
ደህንነታችን የተጠበቀ
ስለሆነ ቤታችን ነው።

ከፍቅር አጋሬ ጋር የተገናኘነው በጣም ልጅ እያለን ነው። ሌሎች ኩዊር ሰዎችን የት እንደምናገኝ ራሱ አናውቅም ነበር። ሁለታችን ብቻ ከአለም ላይ እንደተጋፈጥን ይሰማን ነበር። በአደባባይ ከጓደኝነት ያለፈ ነገር እንደሌለን እያስመሰልን፤ ጥርጣሬ በማይጭር መልኩ አብረን እንራመድ፤ እንስቅ እንጫወት ነበር።

አንድ ምሽት ደስ ከሚል እራት በልተን ወደቤቷ እየሸኘኋት ነበር። ሰፈሯ የመንገድ መብራት ስለሌለው ጨለማ ዙሪያችንን እንደሚስጥር ከቦን ነበር። በሯ ላይ ስንደርስ ደህና እደሪ ብዬ ሳምኳት፤ ለካ እህቷም ወደቤት እየገባች ነበር። በሰአቱ የተሰማኝ ድንጋጤ ዛሬም እንዳዲስ ይታወሰኛል በሚገርም ሁኔታ ግን እህቷ ለእሷም ሆነ ለእኔ ምንም አላለችንም። ይህ ከሆነ አመታት አልፈዋል። ያኔ ነገሮች እንዳሁኑ አልተባባሱም ነበር። አሁን ከሀይ ፋይቭ ያለፈ ነገር አናደርግም።

በፍቅረኝነት ጥቂት አመታት ከቆየን በኋላ ጥሩ ስራ ስላገኘሁ ቤት ተከራይቼ ወጣሁ። አብራኝ ትኖራለች ብዬ አስቤ ነበር ግን የእሷ ቤተሰብ ከኔ ይልቅ ወግ አጥባቂ ነበሩ። ስለዚህ አብሮ መኖር የማይታሰብ ሆነ። እንደመፍትሄ ሁለት ወይ ሶስት ምሽት ከእኔ ጋር ልታሳልፍ ወሰንን። ምን ያህል ልዩነት እንደፈጠረልን መግለጽ አልችልም።

ከረዥም የስራ ቀን በኋላ ወደባዶ ቤት መምጣት ትርጉም የሌለው እና ዝምታ የሞላበት ነበር። ሀሙስ ግን የተለየ ቀን ነው። ጠዋት ስነሳ ጀምሮ በደስታ ነው። ቤቱን አፀዳለሁ፤ አስቤዛ እገዛለሁ፤ እንደምትመጣ በማሰብ ሁሉንም ነገር አስተካክዬ እጠብቃታለሁ። አርብ ማታ እየጠበቀችኝ ሳገኛት ቤቱ በህይወት ይሞላል። የምትወዳቸውን ሙዚቃዎች ከፍታ ትደንሳለች። ተኝቼ ስነቃ አጠገቤ ሳገኛት ደስ ይለኛል።

የእረፍት ቀናችንን ያለንን ምግብ በማብሰል እናሳልፋለን። ምስር፤ ጎመን እና ጥብስ። ቡናችንን እንጠጣለን። ስለሁሉም እና ስለምንም እናወራለን። ከላይ ሲታይ ቀላል ነገር ይመስላል ለእኛ ግን ከምንም በላይ ነው። አለም የማትደርስብንን ቦታ ፈጥረናል። ደህንነታችን የተጠበቀ ስለሆነ ቤታችን ነው። እንደጓደኛ ብቻ መሳቅ አይጠበቅብንም፤ መሳሳም እና መተቃቀፍ እንችላለን። ሌላ ሰው ምን ይለናል ሳንል መተያየት እንችላለን። ወይን እየጠጣን ፊልም እናያለን። ሆረር ፊልም እወዳለሁ፤ እሷ ግን አትወድም። እውነት ለመናገር ስክሪኑ ላይ ያለው ነገር ለውጥ አይፈጥርም፤ ደስታን የሚሰጠኝ በእቅፌ ውስጥ ሆና ስትስቅ እና ፊቷን በእጆቿ ስትደብቅ ማየቴ ነው።

ሁሉም ነገር ቀላል ነው ማለት ግን አይደለም። የራሳችን መደበቂያ ብንፈጥርም ከውጭ ያለው ግፊት ግን አይጠፋም። አበቦች ትወዳለች፤ እና ለቫለንታይን ቀን ቤቱን አጽድቼ፤ ቸኮላት እና አበባ ገዝቼ ሰርፕራይዝ አረኳት። ስትገባ ደስ ብሏት ነበር። ደስ የሚል ጊዜም አሳለፍን። ወደቤቷ ልትሄድ ስትል ግነ አበባውን መውሰድ አልቻለችም። ከየት ነው ያመጣሽው; ማን ሰጠሽ፤ ፍቅረኛሽ ማነው፤ መቸ ነው

የምታገቢው፤ ጥያቄዎቹ አያልቁም። ስለዚህ አበባውን ትንሹ አፓርትመንቴ ውስጥ ትታው መሄድ ነበረባት።

በአላትን አብረን ማሳለፍ አንችልም። ሁለታችንም ቀኑን የምናሳልፈው ከቤተሰቦቻችን ጋር ነው። ካለፈ በኋላ ግን ቤታቸው ሄጄ እንደልብ ጓደኛዋ ከቤተሰቧ ጋር እራት እበላለሁ። ቡና እየጠጣን እናወራለን፤ እንስቃለን። ቀለል ያለ ጊዜ ስለምናሳልፍ ድጋሚ መሄድን እያሰብኩ እለያቸዋለሁ። ሊያውቁም ላያውቁም ይችላሉ። ወደፊት ነገሮች ሊቀየሩ ይችላሉ። ለአሁን ግን ለእኔና ለፍቅሬ የሚስጥር በአላችን ነው።

ሁኔታዎች አስፈሪ እየሆኑ ነው ስለወደፊት ተስፋ እንዳይኖረን ያረጉናል። አንድ ቲክቶከር ሬስቶራንት ውስጥ ፎቶ ቢያነሳን ወይም መንገደኛ የሆነ ነገር ቢያይብን ህይወታችን እስከመጨረሻው ሊቀየር ይችላል። ህዝባችን ራሳችንን ስለሆንን ብቻ ማየት ብቻ ሳይሆን ማሳፈር፤ ማጥቃት እና ማሳደድን የሚመርጥ ነው። እዚህ ሀገር ባሉ ብዙ ሰዎች መቼም ተቀባይነት ላናገኝ እንችላለን። በነዚህ አራት ግድግዳዎች ስር ግን የራሳችንን ነጻ ሀገር መስርተናል። ለእኔ ቤት ቦታ ሳይሆን እሷ ናት።



# ቤተክርስቲያን ህንጻ አይደለም

ስለአለም ያለኝ አመለካከት የተገነባው በቤተክርስቲያን ነው፤ የማውቀው መፅሀፍ ቅዱስ ማንበብ፤ መጸለይ እና እሁድ እሁድ አዲስ አበባ ከሚገኙ ቤተክርስቲያናት አንዱ መሄድ ነው። "የተመረጡት" የሚለው ትምህርት ለእኔ ትልቅ ትርጉም ነበረው። በአለም ላይ ላሉ ሁሉ እንዲድኑ የመጸለይ ግዴታ እንዳለብኝ ይሰማኝ ነበር። ቤተክርስቲያን አለሜ ነበር። አገልግሎቶች ላይ በመሳተፍ፤ ማምለክ እና ከእሁድ ፕሮግራም በኋላ ከልጅነት ጓደኞቼ ጋር መሯሯጥ የሚያስደስቱኝ ነገሮች ነበሩ። እነዛ ቀደም ያሉ በቤተክርስቲን ያሳለፍኳቸው ጊዜያት ቤተኝነት ተሰምቶኝ ያሳለፍኳቸው ናቸው።

ሳድግ እና ስለራሴ መማር ስጀምር ግን እንደቤቴ የቆጠርኩት ቦታ እየተወሳሰበ መጣ። የጾታ መገለጫዬ እንደሌሎች ሴቶች አልነበረም፤ ፍላጎቶቼም እንደዛው። የማውቀው ለሌሎች ሴቶች የነበረኝ ፍላጎት ለማንም የማይነገር እንደነበር ነው። ቤተክርስቲያናት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት እንደማይደግፉ በአደባባይ እንደሚናገሩ ስሰማ ዝምታዬም እየጠነከረ መጣ። በዚህ ጉዳይ ላይ የነበሩ አመለካከቶች በይፋ የሚነገሩ ስለነበሩ ይበልጥ እየፈራሁ መጣሁ። በቤተክርስቲያን ማገልገል እግዛብሄርን መዋሸት መሰለኝ።፡ ሰይጣን ይዞኝ ይሆንም ብዬ አስቤ አውቃለሁ። በጣም ከማፈሬ የተነሳ የማገለግላቸው ሰዎች ፊት መቆም አልቻልኩም። ያለማቋረጥ የሚሰማኝ ከሁሉም ሰው በላይ ሀጥያተኛ እንደሆንኩ ነው። ይህን ሁሉ ነገር የምነግረው ሰው አልነበረኝም። አንድም ሰው ስለግራ መጋባቴ እና የሚሰማኝ ፍላጎት አያውቅም ነበር።

ሳድግ እና ስለራሴ መማር ስጀምር ግን እንደቤቴ የቆጠርኩት ቦታ እየተወሳሰበ መጣ።

ከአገልግሎት መቅረት እና ከቤተክርስቲያን ጓደኞቼ ጋር መራራቅ ጀመርኩ። ከአቅሜ በላይ ሲሆን መሪውን ትምህርት እና ስራ ቢዚ ስላደረጉን መሄድ እንደማልችል ነገርኩ። እውነታው ግን ራሴን ለማራቅ መወሰኔ ነው። ይህም የተለያዩ ስሜቶች በአንዴ እንዲሰማኝ አደረገኝ። አንደኛው እረፍት ነው ምክንያቱም መደበቅ እና ማስመሰል የለብኝም፤ በሌላ በኩል ደግሞ የማውቀው አለም ቤተክርስቲያን ብቻ በመሆኑ ህመምም ተሰማኝ። ህይወትን እንዳዲስ የመማር ያህል ከባድ ነበር።

መሄድ ካቆምኩ በኋላ ያሉት የመጀመሪያ አመታት በጣም ከባድ ነበሩ። ብዙ ንዴት በውስጤ ነበር በተለይም በዙሪያዬ የማየው ለተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች የነበረው ጥላቻ እየጠነከረ ሲሄድ ቤተክርስቲያን እንዲባባስ እንዳደረገ ማወቄ ያበሳጨኝ ነበር። ለአመታት የማውቃቸው የቤተክርስቲያን ጓደኞቼ ጋር ማውራት አቆምኩ። ቤት ብዬ ያሰብኩትን ቦታ ማጣቴ የፈጠረብኝ ሀዘን መፍታት ባለመቻሌ በንዴት የተሞላ ወጣት ሆንኩ። ቤተክርስቲያን አካባቢ ያሉ ሰዎች አጠገብ መሆን እንኳን አልፈለኩም። መዝሙር መስማትም አቆምኩ። ግን ስለኩዊርነቴ ብዙ በተማርኩ ቁጥር በሌላ የአለም ክፍል ከሚኖሩ ኩዊር ክርስቲያኖች ጋር የመተዋወቅ እድል አገኘሁ። አሉ ብዬ የማላስባቸውን መረጃዎች አገኘሁ። ኩዊር ቤተክርስቲያናት፤ ኩዊር የመስጊድ መሪዎች እና እንደእኔ ያሉ ኩዊሮችን የሚቀበሉ



ማህበረሰቦች እንዳሉ ተማርኩ። ናይጀሪያዊ ጌይ ፓስተር፤ ሳውዝ አፍሪካዊ ጌይ ኢማም፤ እና አሜሪካዊ ትራንስ ፓስተር እና ሌሎችም አሉ። እነዚህ መሪዎች እንደኔ ያደጉበትን ቤተክርስቲያን ጥለው የወጡ ናቸው፤ አንዳንዶቹ በጾታቸው ወይም ጾታዊ ዝንባሌያቸው የተነሳ የታገዱም ናቸው።

ታሪካቸውን ማንበብ ከነበርኩበት ስሜት ለመውጣት መነሻዬ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተክርስቲያን ቢናፍቀኝ መመለስ እንደምችል ተሰማኝ። አንድ የገና ምሽት በኩራት ኩዊር ሴትነቴን ሳልክድ ወደልጅነት ቤተክርስቲያኔ ሄድኩ። ሻማ አበራሁ፤ ዘመርኩ፤ ከአገልግሎቱም በኋላ ትቼ ወጣሁ። ከማንም ጋር የማውራትም ሆነ ራሴን የማስረዳት ፍላጎት አልነበረኝም።

ከአስር አመታት በላይ በኋላ አፍሪካ ውስጥ በሚገኝ ሀገር አንድ ሌዝቢያን ፓስተር የምትሰጠውን አገልግሎት የመሳተፍ እድል አገኘሁ። የማይረሳ ጊዜ ነበር። ከተለያየ የህይወት ጎዳና የመጡ ሰዎች ነበሩበት። እንደኩዊር አፍሪካዊ ሴት እዚሁ አህጉር ላይ እምነታቸውን እና ኩዊርነታቸውን ይዘው የሚኖሩ ሰዎች እንዳሉ ማወቁ የብቸኝነት ስሜቴን አቀለለልኝ። ወጣቶች፤ ጥንዶች፤ እድሜያቸው የገፉ ወንድ እና ሴት ኩዊሮች እና ነን ባይነሪ የሆኑ ሰዎች ነበሩ። ህልም የሚመስል ስሜት ነበረው። ፒያኒስቱ የሬንቦው ምልክት አድርገው ሙዚቀኛው ደግሞ የሬንቦስ ጆሮጌጥ አድርገው ማየቴን አስታውሳለሁ። ሰዎች በነጻነት እምነታቸውን እና የጾታ ዝንባሌያቸውን አስታርቀው ማየት ውብ ነበር። ከአገልግሎቱ በኋላ ተጣድፌ መውጣት አልነበረብኝም፤ ቆይቼ፤ ተጫውቼ፤ ከሁሉም ጋር ሻይ ጠጥቼ ነው የሄድኩት።  በነዚህ ቅጽበቶች የልጅነት ጊዜዬን እያስታወስኩ ነበር፤ ቤተክርስቲያን ያለምንም ጥያቄ ቤቴ ነበር። በዚህም ቤተክርስቲያን ህንጻው እንዳልሆነ ተረዳሁ፤ ቤተክርስቲያን ደህንነት የሚያሰሙኝ፤ የሚቀበሉኝ እና የሚረዱኝ ሰዎች ናቸው።

## ኩዊር ቤተክርስቲያናት፤ ኩዊር የመስጊድ መሪዎች እና እንደእኔ ያሉ ኩዊሮችን የሚቀበሉ ማህበረሰቦች እንዳሉ ተማርኩ።

# የነፃነት ቤት

የማላውቀው ቋንቋ
የሚነገርበት ሀገር
ሳርፍ የነበረኝን ስሜት
አስታውሳለሁ። ባህር
አቋርጦ አብሮኝ
የመጣውን ትናንሽ
የቤት ትውስታ
ውስጤ ቢኖርም
ፍርሀት እና ግራ
መጋባት እየተሰማኝ
ነበር።



ባለፈው ክረምት ሻንጣዬን ይዤ ቤቴ ብዬ የማውቃትን አንድ ሀገር ትቼ ወጣሁ። ለብዙ ሰው የሄድኩት ለትምህርት እና የተሻለ ህይወትን ፍለጋ እንደሆነ ብናገርም ውስጤ ግን ነጻነትን ፍለጋ እንደሆነ ያውቅ ነበር። ለአመታት በሀገሬ ቋንቋ አውርቻለሁ፡ የህዝቧን ፊት ተጋርቻለሁ፤ በባህሏ ውስጥ ኖሬያለሁ። ግን የሚገባኝ ቦታ እንደሆነ ተሰምቶኝ አያውቅም። ባህሉ፤ ሀይማኖቱ፤ ጠባብ የሆኑት የማንነት መገለጫዎች ሁሉ በእኔ አመለካከት የሚቀበሉኝ አልነበሩም። እኔም እንደምቀበላቸው እያስመሰልኩ መኖር መቀጠል አልቻልኩም። ስደተኛ እንደሆኑት ቤተሰቦቼ፤ እንደእናቴ እና እናቷ፤ የሚፈልጉትን ህይወት ለመኖር የሚያስችላቸውን ወደፊት ፍለጋ የተወለዱበትን ቦታ ጥለው እንደሄዱት እኔም የእነሱን ፈለግ ተከተልኩ።

የማላውቀው ቋንቋ የሚነገርበት ሀገር ሳርፍ የነበረኝን ስሜት አስታውሳለሁ። ባህር አቋርጦ አብሮኝ የመጣውን ትናንሽ የቤት ትውስታ ውስጤ ቢኖርም ፍርሀት እና ግራ መጋባት እየተሰማኝ ነበር። አየርማረፊያው ውስጥ ባቡር ስጠብቅ የፕራይድ ስቲከር ቦርሳው ላይ የለጠፈ ሰው አየሁ። ለሰከንዶች ተደናግጬ ነበር፤ ሰው እንዳያየው ፈራሁለት። በኋላ ግን ችግር እንደሌለው አስታወስኩ። በመረጋጋት ተነፈስኩ። እዚህ በነጻነት፤ ያለምንም ጥፋተኝነት መተንፈስ እንደምችል ተገለጸልኝ።

የባቡር ጣቢያው አዲስ ህይወትን የተቀላቀልኩበት መነሻ ቦታ ነበር። ጉግል ማፕስን ተከትዬ ሰዎች “የሀበሻ ሰፈር” ብለው ወደሚጠሩት እና ኢትዮጵያውያን የሚበዙባቸው ሬስቶራንቶች እና ሱቆች ወደሚገኙበት ቦታ አመራሁ። የባቡሩ በር ሲከፈት ግን ጣቢያው ከወለል እስከ ጣሪያው በቀስተደመና ቀለም ተሸፍኖ አየሁ። ለአምስት ደቂቃ ያህል በድንጋጤ ቆምኩ። ለተጨማሪ አምስት ደቂቃዎች ደግሞ  በግርምት ሳቅኩ። የሀበሻ ሰፈር የተባለው ቦታ የኩዊሮችም ሰፈር ነው። ውጪ ላይ ከሚገኝ የኢትዮጵያ ሬስቶራንት ፊትለፊት ጓደኛዬን ማግኘት ነበረብኝ። እሱን ተሻግሮ ደግሞ የከተማው ታዋቂ ጌይ ባር ይገኛል። በዛች ቅጽበት መቼም አያለሁ ብዬ የማልጠብቀውን ነገር ተመለከትኩ፤ ባህሌ እና ኩዊርነቴ አብረው ሊኖሩ የሚችሉበት ስፍራ ነበር። በዚህ ቦታ አንደኛው ሌላኛው ዝም ለማስባል አያድንም።

> የእኔ የምንለውን ቦታ መስራት ቤት እንደመስራት ነው። የተለያዩ ክፍሎች አንድ ላይ በማምጣት ደስታ እና ምቾትን እንፈጥራለን።

በቀጣዩ አመት ከተማውን በደንብ እየተላመድኩ መጣሁ። የመጀመሪያዬን ፕራይድ ዝግጅት ተሳተፍኩ። ጮክ ብዬ “ባይ ነኝ” ብዬ መናገር ቻልኩ፤ ያውም ያለምንም ማንሾካሾክ እና ማን ሰምቶኝ ይሆን ፍርሀት! አብሬው የምማረው ሰው ቦርሳዬ ላይ በኩራት ለጥፌ የምዞረው የፕራይድ ስቲከር ሰጠኝ። ወደአፓርትመንቴ በየቀኑ በምመላለስበት መንገድ ላይ መስኮቱ ላይ የፕራይድ ባንዲራ ያለበት ቤት አያለሁ፤ ትክክለኛው መንገድ ላይ እንዳለሁ ማስታወሻዬ ነው። እዚህ ሴቶች ሴቶችን ፤ ወንዶችም ወንዶችን በአደባባይ ያለፍርሀት ሲስሙ ይታያሉ። እዚህ እፍረት የሌለበትን ቤቴን አገኘሁ።

ከመጣሁ ከሁለት ወራት በኋላ የእንጀራ ናፍቆቴ ወደኢትዮጵያ ማህበረሰብ ሳበኝ። እንጀራ በሽሮ ፍለጋ የሀበሾች ዝግጅት ላይ ተገኘሁ። ክፍሉ ከተለያየ የህይወት መንገድ የተገኙ ሰዎች ያሉበት ነበር። ከአመታት በፊት ኢትዮጵያን ለቀው የመጡ እድሜያቸው የገፉ ሰዎች፤ ኢትዮጵያዊ የሆኑ፤ በጉዲፈቻ የሄዱ፤ እንዲሁም

ሀገሪቷን ረግጠው የማያውቁ ሰዎች ነበሩ። በአንዱ ጠረጴዛ እንደኔ ኢትዮጵያዊ ፊት ያላት17 አመት የሚሆናት ልጅ አብረዋት ለመጡ ኢትዮጵያዊ ላልሆኑ ጓደኞቿ ስለእንጀራ እና ሽሮ ስለማያውቀው ባህል እንደሚያወራ ሰው በግራ መጋባት ታስረዳለች።

ለመሄድ ስትነሳ ከጓደኞቿ አንዷን ጎንበስ ብላ ከንፈሯን ሳመቻት፤ ለእሷ የተለመደ ነገር ነበር። ለአንዳንዶች ደግሞ በተቃራኒው። ክፍል ውስጥ የነበረው ድባብ ተሰማኝ፤ በርግጥ ይህ ስሜት የነበረው የኢትዮጵያን የማይነገሩ ህጎች ይዘን በቆየነው ሰዎች ውስጥ ነው። አብዛኞቹ አዲስ የመጡ ተማሪዎች ናቸው፤ እዚህ የኖሩት እና አዲሱ ቤታቸው ያለውን ባህል ተቀብለው የሚኖሩት እድሜያቸው ገፋ ያሉ ሰዎች ምንም አልመሰላቸውም። የተሳሳተ አመለካከት የነበረን በቅርብ የመጣነው ነበርን።

እሷን እየተመለከትኩ ራሴን አየሁ። መቼም የማይቀበላትን ባህል ለመቀላቀል እየሞከረች ነበር። ብዙዎች ለእሷ ያላቸው ጥላቻ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ስላልኖረችው አታውቅ ይሆናል። እኔ በኩዊርነቴ ያልተቀበለኝን ባህል መሸሽ ነበረብኝ። ይህ አዲስ ቦታ ይቀበለኛ እንደሆነ አላውቅም። ምናልባት ያተኮርኩት ኩዊርነቴን መቀበላቸው ላይ ስለሆነ ጥቁርነቴን ችላ ብዬው ሊሆን ይችላል። እሷ ደግሞ በደንብ የማታውቀው ሀገሯ እንዲቀበላት ለማድረግ ስትሞክር እኔ ደግሞ በደንብ ከማውቃት ሀገሬ ነጻነትን ፈለኩ። ግን ሁለታችንም አንዳይነት ጠረጴዛ ላይ ተቀምጠን አንዳይነት ጥያቄ እንጠይቃለን። "ቤታችን ራሳችንን እንዳንሆን ሳይፈቅድልን ሲቀር የኔ የምንለው ቦታ የት ይሆን" የኔ ቤት የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ብቻ እንድሆን እንዳስገደደኝ የሷ ቤት ደግሞ ነጭ እንድትሆን ያስገድዳት ይሆን"

ሁለታችንም ግን የተለያዩትን ማንነቶቻችንን ይዘን ከራሳችን ጋር ሰላም ለመፍጠር እየሞከርን ነው። በዛ ሰአት የእኔ ብለን የምናስበው ቦታ ስለተወለድንበት ወይም ባለን የስጋ ዝምድና ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ተረዳሁ። ለራሳችን ብለን በምናዘጋጀው እና ለመኖራችን ይቅርታ ሳንጠይቅ ሁሉም ማንነታችንን ይዘን የምንኖርበት ቦታ ነው። የእኔ የምንለውን ቦታ መስራት ቤት እንደመስራት ነው። የተለያዩ ክፍሎች አንድ ላይ በማምጣት ደስታ እና ምኞትን እንፈጥራለን። የመጀመሪያው ስራችን ደግሞ መሰረት መጣል ነው። ለእኔ መሰረት ብዬ የማስበው ደህንነትን እና የሚወዱኝ እና በእኔነቴ የሚቀበሉኝን ሰዎች ማግኘት ነበር። ልክ የፕራይድ ስቲከር እንደሰጠኝ ጓደኛ እና የፕራይድ ባንዲራ እንዳለበት መስኮት....

ምናልባት ያቺ ወጣት እና እኔ በተለያየ መንገድ ቢሆንም የአንድ እውነታ መገለጫዎች ነን። ቤት የምንወርሰው ነገር አይደለም። ራሳችን የምንገነባው ነው። ውጪ ባሉ ሰዎች ምክንያት ሀፍረት ሳይሰማን ራሳችን የሰራነው የምንኖርበት ቤት የእኛ ነው።

በዛ ሰአት የእኔ ብለን የምናስበው ቦታ ስለተወለድንበት ወይም ባለን የስጋ ዝምድና ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ ተረዳሁ።



# በስደት ያገኘሁት ቤቴ

እንደኩዊር ለእኔ ቤት ማለት ከቦታ በላይ ነው፤ ደህንነቴ ተጠብቆ ራሴን የምሆንበት አካባቢ ሊሆን ይገባል። በማንነቴ የምከበርበት እና ተቀባይነት የማገኝበትም ነው። ኢትዮጵያ እያለሁ ቤት ማለት ቤተሰቤ የሚኖርበት፤ የለመድኩት ባህል እና ቋንቋ ያለበት ግኡዝ አካል ነበር። ለልቤ ግን ሰላም የሚሰጥ አልነበረም። በውስጤ ትልቅ ሚስጥር ነበር፤ በሌሎች ሴቶች መማረኬ። እንዲቀለኝ ስል ብናገረው እመኝ ነበር ግን ብዙ ፍርሀት እና ምንም እምነት ስላልነበረኝ ሚስጥር ሆኖ ቆየ።

ወደኬንያ የመጣሁት ለእዛ ነው። እዚህ ቤት ለሚለው ቃል አዲስ ትርጉምን አገኘሁለት። አሁን ኬንያ ቤቴ ነው፤ ኢትዮጵያ እያለሁ ከሚሰማኝ የእኔነት ስሜት ይልቅ እዚህ የሚሰማኝ ይልቃል።

የቤተኝነት ስሜት ከተለያየ አይነት ነጻነት ይመጣል። እዚህ ጾታዊ ዝንባሌዬን በነጻነት መግለጽ እችላለሁ። ከፍቅረኛዬ ጋር በአካል ፍቅሬን መግለጽ እችላለሁ። በአደባባይ የመሳም፤ እጇን የመያዝ መብት አለኝ። ሳልደበቅ ዴት መውጣት፤ ዝግጅቶችን ከእሷ ጋር መታደም እና ፍቅረኛ ናት ብዬ ማስተዋወቅ አልከለከልም።

ይህ የደህንነት ስሜት በብዙ አጋጣሚዎች ተሰምቶኛል። አንድ ጊዜ አብሬያት እየተራመድኩ አንድ ሰው “ማነው ሴት ማነው ወንድ” ሲል ጠየቀን። ከመፍራቴ በፊት ሌላ መንገደኛ “ምናገባህ በማያገባህ አትግባ፤ ደህንነት እንዳይሰማቸው ለማድረግ አንተ ማነህ” ሲል ተከላከለልን። በመጨረሻ ሰውዬው ይቅርታ ጠየቀን። በዛች ቅጽበት ኬንያ ውስጥ የሚጠብቁን ኩዊር ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ማህበረሰቡ በአብዛኛው ደህንነት እንዲሰማን እንደሚያደርግ ተረዳሁ።

ሌላ ጊዜ በስራ ቦታዬ የነበሩ ሰዎች ለምን ሌዝቢን እንደሆንኩ ጠየቁኝ። ከወንድ ጋር ሆነሽ ስለማታውቂ ነው ሌላው ጥያቄያቸው ነበር። ሌሎች ደንበኞች ግን “ተሳስታችኋል፤ ራሷን የመሆን መብት አላት፤ የእናንተን ህይወት እየነካች አይደለም፤ ተዋት” ብለው እንዲሄዱ አደረጉ። ኩዊር ካልሆኑ ሰዎች የማገኘው እንዲህ ያለው ድጋፍ ቤቴ እንዳለሁ እንዲሰማኝ ያደርጋል።

የፍቅር ግንኙነቴም ይህን ስሜት አጠናክሮታል። ከፍቅረኛ ጋር መሆኔም የትም ብንሆን ቤት ማለት ምቾት፤ ደህንነት እና የእኔነት ስሜት መሰማት እንደሆነ ተረድቻለሁ።

ኬንያ በምትሰጠኝ ደህንነት በፊት ብሆን ልመሰርት የማልችለውን ህይወት አብሬያት መኖር እችላለሁ። በአንድ ጣራ ስር አብረን እንኖራለን። ግንኙነታች ካለፈባቸው ማህበረሰባዊ ግፊቶች ነጻ ወጥቶ እኩልነት ያለበት ነው። ከምንም በላይ አብረን ያለፍርሃት እና በነጻነት ቤተሰብ ለመገንባት ወስነናል። ከእሷ ጋር የመረዳት እና የመፈቀር ስሜት ይሰማኛል። ቤቴ ናት፤ ኬንያ ደግሞ የምንገነባበት ቦታ ነው።

በስደት ቤትን ማግኘት የተደበላለቀ ስሜት አለው። በዚህ ፍጥነት ደህንነቴ የተጠበቀበት ቦታ በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ። በፊት ማሳለፍ የማልችለውን ጊዜ አሁን እያሳለፍኩ ነው።

ግን ንዴትም ይሰማኛል። በራሴ ሀገር ይህን ተቀባይነት እና ነጻነት ባገኝ ኖሮ ጓደኞቼን እና ቤተሰቤን መተው አይኖርብኝም ነበር።

ቢሆንም በውሳኔዬ አልጸጸትም። ለቤት የነበረኝ ትርጉም አድጓል። የተገነባ ህንጻ ወይም ሀገር አይደለም። ቤት ምቾት፤ ድጋፍ፤ ተቀባይነት እና የእኔነት ስሜት እንዲሰማኝ የሚያደርግ ቦታ ነው። በምገነባቸው ግንኙነቶች እና ባገኘኋቸው ደህንነቴን ባስጠበቁልኝ ቦታዎች ውስጥም ነው። በኬንያ ይህን ቤት ገንብቻለሁ። እዚህ በስደት ቤቴን አግኝቻለሁ።

ራሴ ሀገር ይህን ተቀባይነት እና ነጻነት ባገኝ ኖሮ ጓደኞቼን እና ቤተሰቤን መተው አይኖርብኝም ነበር።





# በግርግር ውስጥ የሰራነው ቤት

በጩኸት አስቴርን
ተቀበልናት።
ፍቅረኛዬ
የአስቴርን
አገባብ እና
የህዝቡን
ምላሽ
በካሜራዋ
እያስቀረች
ከፊትለፊቴ
ነበረች።

ግርግር፤ ጫጫታ፤ ደማቅ መብራት አትወድም። ኧረ ዘፋኙንም አትወደውም። ግን ይኸው በዚህ ሁሉ ውስጥም አጠገቤ ተገኝታለች።

እድል የምትጠላቸውን ነገሮች እንዳለ አንድ ላይ አጣምራ ይሄን ምሽት የሰራችው ይመስላል። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ዲጄው እያጫዋተ ያለውን ታዋቂ አማርኛ ዘፈን አብረው እየዘፈኑ ነው። ለሷ ከቅዠት አይተናነስም፤ ከተለመደው የቅዳሜ ምሽቷ ተቃራኒ ነው።

ወደአዳራሹ ገብተን መድረኩ እንዲታየን በተጠጋን ቁጥር ደህና መሆኗን ለማረጋገጥ እየደጋገምኩ አያት ነበር። እኔና እና ጓደኞችን ዝግጁ ነበር እሷ ደህና ለመሆን እየጣረች ነው።

ዲጄው ሀገርኛ እና ዘመናዊ ሙዚቃዎችን ማጫወቱን ቀጠለ። ፍቅረኛዬ መደነስ ትወዳለች፤ ቀስ በቀስ ዜማው እየሳባት ትከሻዋን ፈታ ማድረግ እና ሰውነቷን ማወዛወዝ ጀመረች። እንደምትዝናናበት ጥርጥር አልነበረኝም። ጥሩ ምርጫ አላት፤ በማይጠበቅ ሁኔታ ሙዚቃ ስትሰማ ደስታን ፈልጋ የማግኘት ተሰጥኦ አላት።

ያሳሰበኝ ዋናው ዝግጅት ነበር። ከብዙ ጥበቃ በኋላ ዳዊት መለሰ መጣ። ደግነቱ በምትወደው ሙዚቃ ጀመረ። እንደውም የተወሰኑ ስራዎቹን አብራው አዜመች። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን በዛባት እና እረፍት ፍለጋ ከጓደኞችን ጋር ወደውጪ ወጣች።

ሙከራዬ እንዳልተሳካ አሰብኩ። ብዙ በቆዩ ቁጥር ምናልባት በጣም ተጫንኳት ብዬ አሰብኩ። ትተነው እንድንሄድ ሳስብ ተመለሱ። ለመቆየት ዝግጁ እንደሆነች ነገረችኝ። ዳዊት አዝናንቷት ነበር። እኔና ጓደኛዬ በደስታ እሷ ደግሞ በመሰላቸት ታላቋን አርቲስት መጠበቅ ጀመርን።

መድረክ መሪዋ አስቴርን "አዲስ አበባ ዝግጁ ናችሁ" በማለት ስታስተዋውቅ አዳራሹ ደመቀ! የሙዚቃው ድምጽ ከፍ አለ፤ መብራቱ ተብለጨለጨ፤ የጭስ ማሽኑም አካባቢውን አፈነው።

ስትገባ የነበረው ድምጽ በመሬት መንቀጥቀጥ መለኪያ ሊለካ ይገባል። ሀገሬ የሚለው ሙዚቃዋ ኖት ሲሰማ ሁላችንም ልናብድ ነበር። ወደ ኮረሱ ስትደርስ ግጥሙ እንደፈተና ተሰጥቶን የነበረ ይመስል ሁላችንም በአንድነት መዝፈን ጀመርን። በጩኸት አስቴርን ተቀበልናት። ፍቅረኛዬ የአስቴርን አገባብ እና የህዝቡን ምላሽ በካሜራዋ እያስቀረች ከፊትለፊቴ ነበረችች።

ከዛ ወደኔ ዞረች።

በዛች ቅጽበት የሆነ ነገር ሲቀየር ተሰማኝ። የሚብለጨለጩት መብራቶች ውብ ፊቷ ላይ በእርጋታ ያረፉ መሰሉኝ። ለግላችን ኮንሰርት የጀርባ ድምጽ

እንደሆነ ሁሉ የህዝቡ ጩኸት የተረጋጋ ዜማ ሆነ፤ የአስቴርም ድምጽ ተደበቀ።

አስቴር ሙዚቃውን ስትጫወት ፍቅረኛዬ በቀስታ እጄን ያዘችኝ፤ በደስታዬ እየተደሰተች፤ እኔ ደግሞ መኖሯን እያመሰገንኩ ነበር። እጃችን በተነካካ ቁጥር የልብ ምቷ ይሰማኛል፤ አለም ቀስ እያለች፤ ዜማው መረጋጋትን ይፈጥራል።

ተያየን፤ እጅ ለእጅ ተያያዝን፤ የመኪና ማቆሚያው ውስጥ ተደብቀን ተሳሳምን። ኮንሰርቱን የራሳችን ያደረግን ሁለት ኩዊር ሴቶች ነበርን። ጩኸት የበዛበት ቢሆንም በዛ ሁሉ ግርግር ውስጥ የግላችንን ጊዜ፤ የእኛ የምንለውን ቤት ሰራን።

## አስቴር ሙዚቃውን ስትጫወት ፍቅረኛዬ በቀስታ እጄን ያዘችኝ፤ … እጃችን በተነካካ ቁጥር የልብ ምቷ ይሰማኛል፤ አለም ቀስ እያለች፤ ዜማው መረጋጋትን ይፈጥራል።

# ቤት የት ነው?

## የሁላችንም ጥያቄ

ለኩዊር ኢትዮጵያውያን "ቤት" ውስብስብ ቃል ነው። በውስጡ የበርበሬ ሽታን ከእናቶቻችን ጸሎት ጋር አጣምሮ ይዟል። በሌላ በኩል ደህንነት ሊሰጡን የሚገቡ ስፍራዎች እውነተኛ ማንነታችን መደበቅ ስላለብ የሚሰማንን ህመምም አለው። ግን ገንቢዎች እኛው ራሳችን ነን። አስበን በማናውቀው መልኩ ቤታችንን እየገነባን እና እያገኘን ነው። ኢትዮጵየዊነታችንን አይቀይረውም፤ የራሳችን ህይወት ቀራጺ ግን ያደርገናል። እናንተስ ቤታችሁን ፍለጋ ያለው ጉዟችሁ ምን ይመስላል?

### ሰሜን፡ ቤት በሰው ውስጥ

በሰው በተሞላ ካፌ ውስጥ በሚስጥር እጅ በመያያዝ የሚገለጽ ፍቅር፤ አለሁልሽ/ህ የሚል አስተያየት፤ ከፍቅረኛ ጋር የሚገነባ ውጫዊ አለምን የሚዘነጋ የግል አለም ነው።

ቤት በሚስጥር በያዛችሁት ጥልቅ ፍቅር ውስጥ ነው።

### ምስራቅ፡ ቤት በመረጥነው ቤተሰብ ውስጥ

በጠባብ ክፍል ውስጥ በተሰበሰቡ ማእድ እና ሚስጥር በሚጋሩ ጓደኞች ውስጥ ነው። 24/7 ከጎናችሁ በሆነው የቴሌግራም ግሩፕ፤ እንደስጋ ዘመዳችሁ ቤተሰብ በምታደርጓቸው ጓደኞች ድጋፍ ውስጥ ፍቅር አለ።

ቤታችሁ የመረጣችሁት ቤተሰብ ነው።

### ደቡብ፡ ቤት በራሳችሁ ውስጥ

የክፍላችሁ ሰላም፤ ቡና አፈላላችሁ፤ በቂ መሆናችሁን የማወቅ እውነት፤ በራሳችሁ ውስጥ የገነባችሁትና መሸማቀቅ የማይገባበት ስፍራ ነው። ቤታችሁ የማይነቃነቀው እናንተነታችሁ ነው።

### ...ምእራብ፡ ቤት በነጻነት ውስጥ

በአዲስ ከተማ እጅ ለእጅ ተያይዞ የመሄድ ጀግንነት ነው። ፍቅራችሁ ወንጀል ባልሆነበት ቦታ የመተንፈስ እፎይታ፤ በብርሀን አዲስ ህይወት የመገንባት ጽናት ውስጥ ፍቅር አለ።

ቤታችሁ ታግላችሁ ያገኛችሁት ነጻነት ነው።



የቤተኝነት ስሜታችሁ ካርታ ልዩ ነው። እየገነባችሁ ነው እንጂ አልጠፋችሁም። ይህ ከምንም በላይ ትልቅ የፍቅር ማሳያ ነው።